Immigratie- en Naturalisatiedienst
*Ministerie van Justitie en Veiligheid*

# ያልተፈለገ ባዕድ መባልህ ለአንተ ምን ትርጉም አለው?

ከኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት (IND) ያልተፈለገ ባዕድ ነህ የሚል መግለጫ ደርሶብሃል። በተቀበልከው ውሳኔ ያልተፈለገ ባዕድ ነህ ተብለህ የተፈረደብህ በምን ምክንያት እንደሆነ ይገልጻል። በዚህ ጽሑፍ ላይ ይህ ያልተፈለገ ባዕድ ነህ የሚል መግለጫ ምን እንደሆነ ኣና ለአንተ ምን ትርጉም እንዳለው ታነባለህ።


1. ያልተፈለገ ባዕድ  የሚል መግለጫ ምንድን ነው?
2. ያልተፈለገ ባዕድ  የሚል መግለጫ ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል?
3. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብህ ምን ማለት ነው?
4. ያንተ መረጃ ከ E&S እና SIS የሚሰረዘው መቼ ነው?
5. አንተ በኔዘርላንድ መኖር ከቀጠልክ ምን ይደረጋል?
6. ያልተፈለገ ባዕድ  የሚል መግለጫ የማትስማማበት ከሆነ ምን ማድረግ ትችላለህ?
7. እንደገና ወደ ኔዘርላንድ መግባት የምትችለው መቼ ነው?
8. ያልተፈለገ ባዕድ  የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ እንዴት መጠየቅ ትችላለህ?
9. ጥያቄ ካለህ ምን ማድረግ አለብህ?


### 1. ያልተፈለገ ባዕድ  የሚል መግለጫ ምንድን ነው?

ያልተፈለገ ባዕድ በሚለው መግለጫ ውስጥ ኣንተ በኔዘርላንድ እንድትኖር እንደማይፈለግ ይገለጻል። ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ የሚሰጥህ IND ኣንተ  ለኔዘርላንድ አደገኛ ነህ ብሎ በሚወስንበት ግዜ ነው። ይህ እርምጃ ብዙውን ጊዜ ከባድ ወንጀል በፈጸሙ ሰዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ነው። ብዙውን ጊዜ የወንጀል ክስ ነው። ያልተፈለገ ባዕድ የሚለው መግለጫ ከተሰጠህ ወዲያውኑ ከኔዘርላንድ መውጣት ኣለብህ። ከዚያ በኋላ ወደ ኔዘርላንድ መግባት አይፈቀድልህም ። ደግሞም ያልተፈለገ ባዕድ ተብለህ መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ ይመዘገባል። ጥያቄ ቁጥር 3 ውስጥ ይህ የመረጃ ስርዓት ምን ማለት እንደሆነ ማብራርያ ታገኛለህ።

### 2. ያልተፈለገ ባዕድ  የሚል መግለጫ ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል?

ያልተፈለገ ባዕድ በሚለው መግለጫ ተግባራዊነቱን የሚያበቃበት ቀን የሌለው ሲሆን የሚቆመው IND ይህን ለማድረግ ሲወስን ብቻ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ያልተፈለገ ባዕድ የሚለው መግለጫ እንዲሰረዝልህ ራስህ ከጠየቅክ ብቻ ነው። ጥያቄ ቁጥር 8 ውስጥ ያልተፈለገ ባዕድ የሚለው መግለጫ እንዲሰረዝልህ እንዴት መጠየቅ እንደምትችል ማብራርያ ታገኛለህ።

### 3. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብህ ምን ማለት ነው?

ያልተፈለገ ባዕድ ነው ተብለህ በመረጃ ስርዓት ውስጥ ተመዝግበሃል። ይህ ማለት ደግሞ መንግሥት ስምህን በመረጃ ሥርዓት ውስጥ ይመዘግባል ማለት ነው። በዚህ መንገድ መንግስት ኣንተ ያልተፈለግክ ባዕድ እንደሆንክ ለማወቅ ይችላል ማለት ነው። ውሳኔው በየትኛው የመረጃ ሥርዓት ውስጥ እንደተመዘገብክ ይገልጻል። ሁለት የመረጃ ስርዓቶች አሉ፥

- *አፈፃፀም እና ምልክት* (E&S)

*ይህ የኔዘርላንድ ፖሊሶችና ድንበር ጠባቂዎች የሚጠቀሙበት የመረጃ ሥርዓት ነው።* E&S መቆጣጠር *የሚችሉት ፖሊሶች እና ድንበር ጠባቂዎች ብቻ ናቸው።*

- *የሸንገን የመረጃ ስርዓት (SIS)*

የሸንገን ሀገራት የድንበር ጠባቂዎች እና ፖሊሶች SIS መቆጣተር ይችላሉ። ኣነሱ ከፈተሹህ በኋላ እንዳትገባ ሊከለክሉህ ይችላሉ። እንዲህ ባለ ሁኔታ ወደ'ዛ ሀገር መግባት አይፈቀድልድም ማለት ነው። የሼንገን አገሮች የትኞቹ እንደሆኑ በ www.ind.nl/schengengebied ወይም www.ind.nl/schengenareaላይ ማንበብ ትችላለህ።

### 4. ያንተ መረጃ ከ E&S እና SIS የሚሰረዘው መቼ ነው?

ያልተፈለገ ባዕድ ነህ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ ማመልከቻ ያቀረብክ ከሆነ እናም ማመልከቻህን ተቀባይነት ካገኘ ሊነሳልህ ይችላል።

## 5. ኣንተ በኔዘርላንድ መኖር ከቀጠልክ ምን ይደረጋል?

ኔዘርላንድ ውስጥ መኖር በህግ ያስቀጣል። እስከ 6 ወር የሚደርስ የእስራት ውሳኔ ሊፈረድብህ ይችላል ወይም በሺዎች ዩሮ የሚቆጠር የገንዘብ ቅጣት ልትቀጣ ትችላለህ። ይህም በወንጀል መቅጫ ሕጉ በአንቀጽ 197 ላይ በዝርዝር ተገልጿል።

## 6. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ የማትስማማበት ከሆነ ምን ማድረግ ትችላላህ?

ተቃውሞህን ወደ IND ማቅረብ ትችላለህ። በተሰጠህ ውሳኔ ውስጥ ይህን ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ ተገልጿል።

## 7. እንደገና ወደ ኔዘርላንድ መግባት የምትችለው መቼ ነው?

IND ያልተፈለገ ባዕድ የሚለውን መግለጫ ከሰረዘልህ እንደገና መግባት ትችላለህ። ይህ የሚሆነው ኣንተ ራስህ እንዲነሳልህ ከጠየቅክ እና ማመልከቻህን በ IND ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው። በጣም ልዩ እና አስቸኳይ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተፈለገ ባዕድ የሚለውን መግለጫ ለጊዜው እንዲነሳልህ መጠየቅ ትችላለህ።

## 8. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ እንዴት መጠየቅ ትችላለህ?

ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ መጠየቅ ትችላለህ። ይህንን ለማድረግ ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ ወይም የመግባት እገዳ እንዲነሳልህ ለመጠየቅ የምትሞላውን ፎርም (9004 ወይም 9504) መሙላት ኣለብህ። ይህ ፎርም በድረ-ገጽ ማግኘት ትችላለህ። እናም ፎርሙን በመሙላት ወደ IND መላክ ኣለብህ። ወይም ደግሞ  ወደ IND ደብዳቤ ትልካለህ። በደብዳቤው ውስጥ ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ (ለጊዜው) እንዲነሳልህ የምትጠይቅበትን ምክንያት ማብራራት ኣለብህ። እንዲሁም የሚከተሉትን መረጃዎች መጻፍ ኣኣለብህ፦

- o ከኔዘርላንድ ለምን ያህል ጊዜ (በተከታታይ) ወጥተህ እንደ ነበር።
- o በዚያ ወቅት ከባድ ወንጀል ፈፅመህ ከሆነ።
- o በአሁኑ ወቅት በወንጀል እየተከሰስክ ያለህ ከሆነ።

ሌላ ሰው ኣንተን በመወከል ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ንዲሰረዝልህ ሊጠይቅልህ ይችላል። ይህ ለማድረግ ግለሰቡን ኣንተን ወክሎ እርምጃ እንዲወስድ ኣኣንተ ሕጋዊ ፈቃድ መስጠት አለብህ። ይህ ወረቀት ላይ በማስፈር ፊርማህን በማኖር ነው የምታደርገው። ይህ ውክልና ስልጣን ተብሎ ይጠራል። ይህ ውክልና ስልጣን እና ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲሰረዝልህ የሚጠይቅ ማመልከቻ ኣንድ ላይ በማድረግ መላክ ኣለብህ።

ፎርሙን ወይም ደብዳቤውን ወደሚከተለው ኣድራሻ ላክ፥
IND Titel en Identiteit
Postbus 10
9560 AA Ter Apel

*ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ኣንዲሰረዝ ማድረግ ፐሚቻሉ ሁኔታዎች*

- በቤተሰብህ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ስላሉ ኣናም ኣንተ ወደ ኔዘርላንድ መምጣት የግድ በሚሆንበት ግዜ።
- ኣንተ በፍርድ ቤት ጉዳይ ላይ መመስከር ስላለብህ ወደ ኔዘርላንድ መምጣት የግድ በሚሆንበት ግዜ።
- በኔዘርላንድ የወንጀል ክስ ስላለህ ወደ ኔዘርላንድ መምጣት የግድ በሚሆንበት ግዜ።
- ይህ ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ የአውሮፓ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌን (ECHR) የጣሰ ከሆነ።
- ከዚህ በፊት ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ከተሰጠህ በኋላ በኔዘርላንድ የመኖሪያ ፈቃድ ያገኘህ ከሆንክ።

*ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ኣንዲሰረዝ የሚያስፈልጉ ሰነዶች*

ፎርሙን ወይም ደብዳቤውን በምትልክበት ወቅት የሚከተሉትን መረጃዎች እና ሰነዶች ላክ፥

- በኣንተ ሁኔታ ውስጥ ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ መነሳት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ማብራሪትት ኣለብህ።
- የተሟላ የግል መረጃዎችህ እና ቀደም ሲል (በሌላ ኣጠራር) ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች መጠርያ ስሞችህ።
- ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ከተሰጠህ ግዜ ጀምሮ የተሰጡህ ፓስፖርቶች የሁሉም ገጾች ቅጂ። ወይም ደግሞ ለመጓዝ እና ድንበር ለመሻገር የተጠቀምክባቸው የሌሎች ሰነዶች ቅጂ።
- ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ከተሰጠህ ቦኋላ የኖበርክባቸውን አገሮችና ቦታዎች የሚያሳይ ኣጠቃላይ ዝርዝር እና ማስረጃ። ይህም ደግሞ ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ኣንዲነሳልህ ማመልከቻውን በምታቀርብበት ወቅት ከአውሮፓ ኅብረት ውጭ እንደምትገኝ እንደ ማስረጃ ልያገለግል ይችላል። ወይም መኖር ወደ ተፈቀደልህ ሌላ የ አውሮፓ ኅብረት አገር ወይ የአውሮፓ የኢኮኖሚ ዞን ሀገር ኣንደ ተመለስክ ያሳያል ማለት ነው። በ www.ind.nl/eueer እና www.ind.nl/en/eueea የ EU/EER ሃገሮች ምን እንደሆኑ ማንበብ ትችላለህ።
- ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ ከተሰጠህ ቦኋላ ከኖበርክባቸው ከእያንዳንዱ አገር መንግስት የተሰጠህ ህጋዊ ሰነዶች። ይህም በአገሪቱ ውስጥ ምንም ዓይነት ከባድ ወንጀል እንዳልፈጸምክ የሚገልጽ መሆን ኣለበት። እናም በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ ውስጥ የወንጀል ክስ እንደሌለህ የሚገልጽ መሆን ኣለበት።

- ለግዜው ወደ ኔዘርላንድ ልትገባ የሚያስገድድህ ሁኔታ ካለ የሚከተሉትን መረጃዎች መላክ ኣለብህ፥
    - o ወደ ኔዘርላንድ የምትመጣበት ቀን እና በኔዘርላንድ የምትቆይበት ቦታ።
    - o የምትገባበት እና የምትወጣበትን የበረራ ቁጥር።
    - o በኔዘርላንድ የምትቆይባቸውን ቦታዎች ሁሉ የሚያሳይ ዝርዝር። ስለ ቆይታህ ሆነ ስለምታደርጋቸውን የገንዘብ ወጪዎች በሚመለከት በግልጽ የሚያሳዩ ማስረጃዎች።
    - o የወንጀል ጉዳይ በሚመለከት፥ የወንጀል ጉዳዩ የደረሰበት ሁኔታ እና የወንጀሉ ጉዳይ አካሄድ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ።
- ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ ማመልከቻ ልያቀርብልህ ለሌላ ሰው የውክልና ስልጣን የሰጠህ ከሆነ፤ ፊርማህን ያኖርክበት የውክልና ስልጣን።

ህጋዊ የውጭ ኣገሮች ሰነዶች ወደ ኔደርላንድስ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ ወይም ጀርመንኛ ቋንቋ ማስተርጎም ኣለብህ። ስለ ሰነዶች ህጋዊ ማድረግ እና ስለ ማስተርጎም በሚመለከት በ www.ind.nl/legalisatie-vertaling ወይም www.ind.nl/legalisation-translation ማንበብ ትችላለህ።

### 9. ጥያቄ ካለህ ምን ማድረግ አለብህ?

- www.ind.nl/ongewenstverklaring ወይም www.ind.nl/en/undesirability የሚሉ የኛ ድረ ገጻች ጎብኝ።
- ወደ የ IND የመረጃ መስመር የስልክ ቁጥር +31 88 043 04 30 ተጠቅመህ ደውል። ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 09:00 ሰዓት እስከ 17:00 ሰዓት ድረስ ባለው ግዜ መደወል ትችላላችሁ።

*ከዚህ ጽሑፉ ይዘት ምንም ዓይነት መብት ማግኘት አይቻልም። ትርጉሙ ወደ ትርጓሜ ልዩነት የሚያመራ ከሆነ በኔደርላንድስ ቋንቋ የተዘጋጀውን ጽሁፍ ነው ወሳኝ የሚሆነው። ምንጩ በመጥቀስ እዚህ እትም ላይ የሚገኘውን ጽሑፍ ለሌላ ጥቅም ሊውል ይችላል።*